# የጌታ መለወጥ በቅዱሱ ተራራ



ታቦርና አርሞንዔም በስምህ ደስ ይላቸዋል (መዝ ዳዊት89፥12)። ይኸ ትንቢታዊ ቃል የተነገረው ከ3000 ዓመታት በፊት በቅዱስ ዳዊት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲያስተምር ሳለ ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን። ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ። እነርሱም አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ ፥ ሌሎችም ኤልያስ ፥ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት። እርሱም እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ  ትላላችሁ? አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ ፤ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ (ማቴ 16፥13-17)።  እንዲሁም ከዚያን ቀን ጀምሮ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር (ማቴ 16፥21-23)።

ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው። በፊታቸውም ተለወጠ ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። እነሆም ፥ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው።  ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን ፤ ጌታ ሆይ ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው ፤ ብትወድስ ፥ በዚህ ሦስት ዳስ አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ አለ። እርሱም ገና ሲናገር ፥ እነሆ ፥ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው ፥ እነሆም ፥ ከደመናው ፤ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው ፤ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ። የእግዚአብሔር አብ ድምጽ ከሰማያት የምወደው ልጄ ይኼ ነው እሱን ስሙት ብሎ ሲናገር ይኼ ሁለተኛው ጊዜ ነበር። የመጀመሪያው ወንጌለ መንግሥትን ከመጀመሩ በፊት በዮርዳኖስ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ ነበር (ማቴ 3፥7 ፣ማር 1፥11 ፣ሉቃ 3፥22)። ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው በፊታቸው ወደቁ እጅግም ፈርተው ነበር። ኢየሱስም ቀርቦ ዳሰሳቸውና ፤ ተነሡ አትፍሩም አላቸው። ዓይናቸውንም አቅንተው ሲያዩ ከኢየሱስ ብቻ በቀር

ማንንም አላዩም። ከተራራውም በወረዱ ጊዜ ኢየሱስ ፤ የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያያችሁትን ለማንም አትንገሩ ብሎ አዘዛቸው። በቤተልሔም ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእኛ እንደ አንዱ በመሆኑ ፤ አምላካዊ ኃይልና ግርማውን ከማሳየት አላገደውም።

በሦስቱም ወንጌላት ላይ ጌታችን በተራራው ላይ በተለወጠ ጊዜ አብረውት የወጡትን የሦስቱን ሐዋርያት ስም እና እነርሱም ምስክር እንደሆኑ ዘርዝረው ጽፈዋል። ከሐዋርያቱም በተጨማሪ ሌሎች ሦስት ምስክሮች ከሰማይ ሙሴ ፤ ኤልያስ እና የእግዚአብሔር አብ ድምጽ መሰማቱ ተጽፏል። ስለዚህ በኦሪት ዘሌዋውያን ላይ ምንም ዓይነት ነገር በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች አፍ ከተነገረ ይጸናል (ዘሌ19፥15) እንደተባለው ከመሬት ሦስት ፤ እንዲሁም ከሰማይ በተገኙ በሦስት ምስክሮች የጌታ አምላክነትና መገለጥ ተረጋግጧል። እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በሁለተኛ መልእክቱ ላይ «የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ 2ኛ ጴጥ 1፥16።»

የሙሴና ኤልያስ በዚያ ተራራ ላይ ከጌታ ጋር መገለጥ የሕግንና የነቢያት ምሳሌ ነው። ክርስቶስ ደግሞ የሕግና በብሉይ ኪዳን የተተነበዩ ትንቢቶች ፈጻሚ መሆኑን ነው። በተጨማሪም ጌታችን ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር እንዲገለጹ ያደረገበት ምክንያት ቀደም ብሎ ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ሲጠይቅ አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ ፥ ሌሎችም ኤልያስ ፥ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ ስላሉት ፥ እርሱም ደግሞ የእነርሱ አምላክ እንደሆነ ለሐዋርያቱ ሊያሳያቸው ፈልጎ ነው።

እንዲሁም ደግሞ ሙሴ በሕይወት ሳለ እግዚአብሔርን እባክህ ክብርህን አሳየኝ ብሎ ለምኖት ነበር ነገር ግን ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም ብሎት ነበር (ዘጸ 33፥17)። ይሁን እንጂ ከዘመናት በኋላ ታላቁ እግዚአብሔር በዚያ ተራራ ላይ ምኞቱን ፈጽሞለታል።

አባ ጊዮርጊስም በመድሐፈ ምስጢር ላይ «ጌታችን በታቦር ተራራ ከነቢያት አንድ ድንግል ፣ ከሐዋርያትም ሁለት ደናግል ፣ ከነቢያት አንድ ያገባ ፣ ከሐዋርያትም አንድ ያገባ አመጣ አለቅነትን ግን ባገቡት ዘጸና ፤ ሙሴ የነቢያት አለቃ ነው ጴጥሮስም የሐዋርያት አለቃ ነው ይኸም የሆነበት ደናግል ባገቡት ላይ እንዳይመኩ እግዚአብሔር በጥበቡ ያደረገው ሥርዓት ነው» ሲሉ ጽፈዋል (መድ ፣ ምስጢር 30፤25)።

ጌታ በዚያ ቅዱስ ተራራ ላይ ለእነዚያ ሦስቱን ሐዋርያት የተገለጸላቸው ፤ በእርሱ ላይ ያላችውን እምነት ፍጹም ለማድረግ ነው። እንዲሁም እኛ ጌታ በሕይወታችን ከጠየቅነው ፤ እርሱ ለመንገዳችን ብርሃንና በእምነታችን ላይ እንድንፀናና ያለንን ጥርጣሬ ፈጽሞ ያስወግድልናል። ወደ ላይ ሰማይም አንቅተን ወደ እርሱ ስንጸልይ ልመናችን ሕይወታችንን እንዲባርክልን ፤ እንደ ቅዱስ ቃሉ እንድንኖር ፤ ለሌሎችም ምሳሌ እንድንሆንና በእኛ ላይ የእርሱ ዕፁብ ድንቅ ሥራ እንዲገለጽ ሊሆን ይገባል።

እነዚያ ቅዱሳን ሐዋርያት በዚያ ቅዱስ ተራራ ላይ የሰው አእምሮ ሊያስበው ከሚችለው በላይ የተፈፀመውን አስደናቂ ተአምር ባዩ ጊዜ ፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን ፤ ሦስት ዳስ አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱንም ለኤልያስ በእዚህ እንሥራ ማለቱን እናስተውላለን። ያንን አስደናቂ ተአምር ሲመለከት ጴጥሮስ እሱ ስለሚያድርበት ምንም አላሳሰበውም ግን በእንደዚያ ባለ ውብ ስፍራ ከተገለጹት ጋር መኖርን መውደዱን እናያለን። ከዚህ ምንማረው እኛም ከጌታ ጋር ስንሆን ፤ ፍጹም እውነተኛ ሰላም እንደሚኖረንና የዚህ ዓለም ደስታ ምናችንም እንዳልሆነ ነው።

ስለዚህ በዚያ ተራራ ላይ በግርማ የተገለጠው ጌታ በበረከቱ እንዲጎበኘንና እሱን እንዲገልጽልን ፤ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ከተናገረው "የሚወደኝ ቃሌን ይጠብቅ ፤ አባቴም ይወደዋል ፤ቃሌን የጠበቀ ቢኖር እኔ ፣ አብ ፣መንፈስ ቅዱስ ወደ እርሱ መጥተን በርሱ ዘንድ እናድርበታለን" (ዮሐ 14 ፣23) ያለውን መፈጸም ይኖርብናል።

እኛም እንደ ሐዋርያቱ ሁሉ ቃሉን ልንጠብቅና የመንግሥቱን ዜና ለሌሎች ልናስተምርና ልንነግር ያስፈልጋል። ሁሉም የየራሱ ስጦታ ስላለው ተሳትፏችን በመዘመር፣ በመስበክ፣ ወይም ደግሞ ከበሰተኋላ ሆነን በተለያዩ ነገሮች ሊሆን ይችላል። ይኸንንም ስናደርግ በእምነት፣ በተስፋ፣ በፍቅር፣ በትህትና፣ ለእርሱ ክብር ሊሆንና፤ የጌታ መንግሥት መምጫው መድረሱን ማሳወቅ ይኖርብናል። አሁንም በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ ለእርሱ አሁንም እስከ ዘላለምም ቀን ድረስ ክብር ይሁን አሜን (2ጴጥ 3፤18)።

## <u>የበዓሉ ምንባባትና አከባበር</u>

የጌታ መገለጥ ወይም በተለምዶ ቡሄ ተብሎ የሚጠራው በዓል የሚከበረው በፍልሰታ ጾም ወቅት ነሐሴ 13 ቀን ነው ፤ ይኸ በዓል ከዘጠኙ ዐበይት የጌታ በዓላት አንዱ ነው።

### <u>የዕለቱ ምንባባት ፤</u>

**የጠዋት**፤ **መዝ ዳዊት** 67(68)፤ 15-16
**ወንጌል ማቴ** 17፤ 1-14

### <u>የቅዳሴ ምንባባት ፤</u>

**ዕብ** 11፤ 23-30
2ኛ **ጴጥ** 1፤15 - **መጨረሻ**
**ሐዋ** 7፤ 34-51
**መዝ ዳዊት** 88(89)፤ 12-13
**ሉቃ** 9፤ 28-38
**አኮቴተ ቁርባን ዘእግዝእትነ/ዲዮስቆሮስ**

እንደ ሀገራችን ባሕል በዓሉ በዋዜማው ሕፃናት ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት እየዞሩ በዓሉን የተመለከተ መዝሙር ይዘምራሉ። እረኞችም ከ2ሺህ ዓመት በፊት በዚያ ቅዱስ ተራራ ላይ ቅዱሳን ሐዋርያቱ ጌታ ሲናገር የሰሙትን ድምፅ በማሰብ ጅራፍ ከቃጫ ሰርተው ያጮኻሉ። እንዲሁም በምሽቱ ላይ ብዙዎች ችቦ በማብራት ጌታ ወደ ብርሃናዊ መለኮትነት መለወጡን ያስባሉ።

በገጠሪቱ ሀገራችንም የቆሎ ተማሪ በመባል የሚታወቁትም ይኸን በዓል ለማክበር ከፍተኛ ድግስ አዘጋጅተው ምዕመናንን፤ የአካባቢውን ሕዝብ በመጋበዝ ያከብሩታል። እነዚህ ተማሪዎችን በዓሉን ለየት ባለ ሁኔታ የሚያከብሩበት ዋናው ምክንያት ሐዋርያት ቤታቸውን ትተው ክርስቶስን እን ደተከተሉት ሁሉ፤ እነርሱም ጌታን ለማገልገል ቤታቸውን ትተው እሱን በመከተላቸው ነው። እነዚህ ተማሪዎች ከቤተሰባቸው ጠፍተው ራቅ ወደ አለ ሀገር ተጉዘው በገዳማትና በአካባቢው በመጠጋት መንፈሳዊ ትምህርትን እየተማሩ ቤተ ክርስቲያናቸውን ያገለግላሉ። እንደ ሐዋርያቱ ሁሉ እነርሱም ስለሚበሉት ስለሚጠለሉበት አምላካቸው እንደሚሰጣቸው በማመን ለትምህርት ይሰደዳሉ። በሚደርሱበትም ቦታ ያሉ ምእመናን እነዚህ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ የሚሰጧቸውን እየተመገቡ ትምህርታቸውን ይቀጥላሉ።

## <u>ጌታ የተለወጠው በታቦር ወይስ በአርሞንኤም ተራራ?</u>

ታቦር በገሊላ አውራጃ ከናዝሬት ከተማ 9ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ረጅም ተራራ ነው። አርሞን ኤም ደግሞ ከታቦር ተራራ በስተ ሰሜን በኩል 32 ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ ሌላ ረጅም ተራራ ነው። እነዚህ በሰሜኑ የእስራኤል ክፍል የሚገኙ ሁለት ታላላቅ ተራራዎች በተለይ በአዲስ ኪዳን የሚታወቁት ከላይ እንደተገለጸው ጌታ በሐዋርያቱ ፊት በግርማ ሞገስ በመገለጡ ነው። ይኸ አስደናቂ ተአምር የታየበት ተራራ ግን የታቦር ወይም የአርሞንኤም ይሁን እስከ አሁን አከራካሪና መልስ ያላገኘ ጥያቄ ነው።

ይሁን እንጂ እ.አ.አ በ348 ዓም የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ የነበረው ቄርሎስ ጌታ የተገለጠበት ተራራ ቢሆን የሚመርጠው ታቦርን እንጂ አርሞንኤምን ስላልሆነ በዚያው ክፍለ ዘመን የመጀሪያውን ቤተ ክርስቲያን በታቦር ተራራ ላይ ተሠራ። ከዚያ ጀምሮ ምእመናን ወደዚያ በመሄድ ያን ታሪካዊ ቦታ በመንብኘት ከበረከቱ ይሳተፋሉ።

በእደ ማርያም እጅጉ ረታ

ነሐሴ 2002